# ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

| | |
|---|---|
| ተዛማጅ ግብአቶች፡- | ABA-RB, AFA-RA, BBB, CNA-RA, DJA-RA, GAA, GGA-RA, IGK-RB, IGT-RA, KGA-RA |
| Responsible Office: | Chief Operating Officer<br>Chief Academic Officer<br>Deputy Superintendent of School Support and Improvement |

## የሠራተኛ የጥቅም ግጭት Employee Conflict of Interest

I. ዓላማ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለላቀ የስነምግባር እና ሙያዊ ብቃት ደረጃን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። ይህ ደንብ (በሜሪላንድ የስነምግባር ህግ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ BBB ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ ስነምግባር) የሚጠበቅ መስፈርትን እና ለ MCPS ሠራተኞች በባህሪያቸው ላይ የፍላጎት ግጭቶችን ለማስቀረት እና የፍላጎት ግጭት በሚፈጠር ጊዜ ሊወሰዱ ስለሚገቡ እርምጃዎች መመሪያዎችን ያብራራል።

II. ዳራ-BACKGROUND

A. ሁሉም ሠራተኞች ከሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ በሁሉም ደረጃ ከሚገኙ ባልደረቦች፣ እና ከማህበረሰብ ጋር በከፍተኛ አንድነት/ሐቀኝነት እና የሙያ ስነምግባር ግንኙነት እንዲኖራቸው ይጠበቃል።

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች በዚህ ደንብ እና በቦርድ ፖሊሲ-Board Policy BBB መሠረት ስለ ሥነ ምግባርማወቅ እና ማክበር እንዳለባቸው እና የእነርሱ ባህሪይ እና ተግባር ከቦርድ ፖሊሲዎች ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ በራሳቸው ኃላፊነት ስለመውሰድ እና የፍላጎት/የጥቅም ግጭትን መፍጠር እንደሌለባቸው፡-

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ሥራዎቻቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት በከፍተኛ ደረጃ የህዝብ እምነት የሚጣልበት አድሎአዊ ያልሆነ ነፃና ፍትኃዊነት የሰፈነበት አሠራርን ለማጎልበት፣ እና

2. ተግባሮቻቸውን ለመፈፀም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)ን ንብረትና ሀብት-ሪሶርሶችን ህብረተሰብን በሚጠቅም ተገቢ አጠቃቀም ላይ ማዋል።

C. ማድረግ ለሠራተኛ እንደ ጥቅም ግጭት ይቆጠራል

1. ከተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ሠራተኞች፣ ወይም ከትምህርት ቤት ሲስተም ጋር ቢዝነስ ከሚሠሩ ሌሎች ጋር የሚኖር ግንኙነትን ለግላዊ ጥቅም ወይም ሌላውን ሰው ወይም ለሌላ ድርጅታዊ አካል እንደ ጥቅም ማግኛ እድል አድርጎ መውሰድ፣ ወይም

2. የሥራ ቦታ ኃላፊነታቸውን፣ የ MCPS ሪሶርሶችን፣ እና/ወይም ምስጢራዊ ወይም በትምህርት ቤት ሲስተም ባላቸው ኃላፊነት ምክንያት የተገኙ መረጃዎችን ለግላዊ ጥቅም ወይም ለሌላ ግለሰብ ወይም ለሌላ ድርጅት አካል መጠቀሚያ ማድረግ።

D. ሠራተኞች ሊሆን የሚችል የጥቅም ግጭትን ወይም የጥቅም ግጭት ይፈጥራል ብለው የሚሰጉበት ባህርይ ካለ በቅድሚያ መመሪያ እንዲጠይቁ ይፋ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ።

E. የጥቅም ግጭቶችን የሚመለከቱ ሁሉም ነገሮች እዚህ ደምብ ላይ አልተዘረዘሩም። በዚህ ደንብ ላይ ያልተጠቀሱ ጉዳዮች ከሆኑ፣ ወይም የትርጉም ጥያቄዎች ካሉ፣ መመሪያ መጠየቅ ያለበት ከ..

1. ርእሰመምህር(ት)፣ ወይም ሱፐርቫይዘር፣ እንደአግባብነቱ፣ ከዚያም

2. ዋና የሥራ ኃላፊ/ተወካይ-chief operating officer/designee ርዕሰመምህራን ወይም ሱፐርቫይዘሮች ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሏቸው፣ ወይም፣ Policy BBB ላይ በተደነገገው መርህ መሠረት ከስነምግባር ኦፊሰር-ethics officerEthics-ስለ ስነምግባር፣ በጥያቄ የተነሣው ጉዳይ በቦርድ መርህ-Board Policy BBB ላይ የተመለከተ ከሆነ።

## III. ትርጉም

A. የቅርብ ቁጥጥር ሰንሰለት ማለት የመምራት ወይም የእለት ተእለት ሥራን የመቆጣጠር ኃላፊነት ላለው-ላላት ሰው የሠራተኞች ተጠሪነት ማለት ሲሆን፣ እና/ወይም ሠራተኛን መገምገም ወይም ወደ ሠራተኛ ግምገማ የሚያመራ ክትትል ማድረግ ነው።

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) resources-ሀብትና ንብረት ማለት በህዝብ ገንዘብ ተገዝተው የ MCPS ንብረት የሆኑ እና/ወይም MCPS ሥራ የሚሠራባቸው ንብረቶች፣ በዚህ የሚወሰን ሳይሆን፣ ንብረቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ተሽከርካሪዎች፣ የሥራ መሣሪያዎች፣ ግብአቶች፣ እና የአእምሯዊ ኃብት ባለቤትነት፣ ሥርዓተትምህርትን ጨምሮ እና/ወይም ሌላ የባለቤትነት መብት ወይም ምስጢራዊ መረጃዎች ናቸው።

## IV. GUIDELINES FOR AVOIDING CONFLICT OF INTEREST - የጥቅም ግጭትን ስለማስወገድ መመሪያ

A. ከተቆጣጣሪነት/ከመሪነት የሚጠበቅ ሚና

1. የተቆጣጣሪነት/የመሪነት ሚና ያላቸው ሠራተኞች

በተቆጣጣሪነት ወይም በመሪነት ቦታ ላይ የሚገኙ የ MCPS ሠራተኞች በቅርብ የቁጥጥር ስንሰለት ስር ያሉትን የትዳር አጋር፣ ዘመድ[1]፣ አማች፣ወይም ጾታዊ ግንኙነት ያላቸውን ማንኛውንም ሌላ ሰው አይቆጣጠሩም። ተቆጣጣሪ የሆነ(ች) የ MCPS ሠራተኛ በእርሱ(ሷ) የቁጥጥር ዕዝ/ሰንሰለት ሥር የሚገኝ/የምትገኝ ሻጭ/አገልግሎት አቅራቢ ወይም ኮንትራክተር የሆነ/ች የትዳር ጓደኛ፣ ዘመድ፣ አማች፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ጾታዊ ግንኙነት ያለው-ያላትን ሠራተኛ አይቆጣጠርም-አትቆጣጠርም።

a) የትዳር ጓደኞቻቸውን፣ ዘመዳቸውን፣ አማቻቸውን፣ ወይም ጾታዊ ግንኙነት ያላቸውን ማንኛውንም ሰው የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ ከተፈጠረ፣ የ MCPS ሱፐርቫይዘሮች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ወይም ኃላፊነት የተሰጣቸው መሪዎች ለቅርብ ሱፐርቫይዘራቸው

---

[1] ዘመድ "Relative" የቤተሰብ አባል ወይም ልጅን ይጨምራል።

ማሳወቅ አለባቸው፣ የቅርብ ሱፐርቫይዘራቸውም ሁኔታውን ለ "Office of Employee Engagement and Labor Relations" ማሳወቅ ይኖርበ(ባ)ታል።

b) አግባብነት ባለው-ባላት የሥራ መሪ አማካይነት ሠራተኛው(ዋ)ን የመቆጣጠር ኃላፊነት ለሌላ ሱፐርቫይዘር መስጠቱን የሚረጋገጥ እርምጃ ይወሰዳል፣ ወይም ትምህርት ቤቱ ወይም ቢሮው እንደሚፈልገው የመቆጣጠር ሃላፊነቱ ለሌላ ሠራተኛ ይሰጣል።

2. ሱፐርቫይዘሮች በኃላፊነታቸው ሥር ከሚገኙ ሠራተኞች ጋር ግላዊ የገንዘብ ጥቅም፣ ወይም ለትዳር ጓደኛ ጥቅም፣ ለዘመድ፣ ለአማች፣ ወይም ጾታዊ ግንኙነት ላላቸው ማንኛውም ሰው የግል ጥቅም የሚሆን የገንዘብ ጥቅም ግንኙነት አይኖራቸውም።

B. በትምህርት ቤት የሚማሩ የሠራተኞች ልጆች

1. የአንድ ተማሪ ቋሚ መኖሪያ ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ክልል ከሆነ(ች)፣ በ Change of School Assignment (COSA) የፀደቀለ(ላ)ት ከሆነ፣ ወይም ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ክልል ነዋሪ ሳይሆን-ሳትሆን እንዲገባ/እንድትገባ የተፈቀደለ(ላ)ት እና የትምህርት ክፍያ ተከፍሎ ከሆነ ወይም እንዳይከፈል የተተወለ(ላ)ት ከሆነ ብቻ ተማሪ ው(ዋ) ወላጅ ወይም ዘመድ በሚሰራበት/በምትሰራበት ት/ቤት መከታተል ይችላል-ትችላለች። እንደዚህ አይነቱ ጥያቄ ሊፀድቅ የሚችለው ሌላ አማራጭ ከሌለ እና የጥቅም ግጭት የማይኖርበ(ባ)ት ሱፐርቫይዘር አማካይነት ከተወሰነ ብቻ ነው።

2. በተቻለ ጊዜ ሁሉ፣ በሠራተኛው(ዋ) እና በልጅ መካከል እንዲሁም ከሠራተኛ የሥራ ኃላፊነት መካከል የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ማናቸውንም ሊሆን የሚችል ወይም የሚታሰብ የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ ስለ ተማሪው(ዋ) ውሳኔ ወይም ሙያዊ ግብአት የመስጠት ኃላፊነትን ወደ ሠራተኛው(ዋ) የቅርብ ተቆጣጣሪ ማስተላለፍ ይገባል።

3. ሌላ አማራጭ ካልኖረ በስተቀር ልጁ/ልጅቱ ወላጅ/ሞግዚት ወይም ዘመድ በሚያስተምሩበት ክፍል መመደብ የለበ(ባ)ትም። ምንም ሌላ አማራጭ ከሌለ፣ ስለ ልጁ - ስለልጅቱ የትምህርት እቅድ የሚዘጋጀው በሠራተኛ፣ የእርሱ(ሷ) ሱፐርቫይዘር፣ እና በትምህርት ቤት አስተዳዳሪ አማካይነት ይሆናል።

C. ሰዎችን፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ወይም ሌላ የ MCPS ሪሶርሶችን ለግል ጥቅም ማዋል

1. ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች በሃላፊነት የሚቆጣጠሩትን ወይም የሚመሩትን ወይም የሚያስተዳድሩትን ማንኛውንም ሰው፣ ገንዘብ፣ ንብረት፣ ወይም ሌላ የ MCPS ሪሶርሶችን ለግላቸው የጥቅም ማግኛ፣ ወይም ለሌላ ግለሰብ ወይም ለሌላ አካል-ድርጅት መጠቀሚያ አያደርግም-አታደርግም፣ ሠራተኞች አልፎ አልፎ ወይም በውስን ሁኔታ የ MCPS እቃ ወይም ፋሲሊቲ በግል የሚጠቀሙ ካልሆነ—

a) የአጠቃቀሙ ወጪ/ዋጋ ለ MCPS እምብዛም ግምት ዉስጥ የማይገባ ከሆነ፣

b) አጠቃቀሙ ከሠራተኛው(ዋ) መደበኛ ሥራ ጋር የማይጣረስ ወይም በሌላ ሠራተኛ መደበኛ ሥራ አፈጻጸም ላይ ጣልቃ የማይገባ/ የማይጋጭ ከሆነ፣ እና

c) አጠቃቀሙ ከማናቸውም የቦርድ መርህ ወይም የ MCPS ደምብ ጋር የማይጋጭ ከሆነ።

2. በዋና የሥራ ኃላፊ ስምምነት ላይ ያልተገለጸ ከሆነ፣ የ MCPS ተሽከርካሪዎች ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ለ MCPS ሥራ ብቻ ነው። ሌሎች ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አገልግሎት ብቻ የሚውሉ የ MCPS መሣሪያዎች የሚያካትቱት፣ የማሽን መሣሪያዎች፣ የፅዳት እና መቀቢያ መሣሪያዎች፣ እና በአገልግሎት የሚያረጁ መሣሪያዎች በሙሉ ናቸው።

D. ስራ

1. የዉጪ ሥራ/ከሥራ ቀን ውጭ መሥራት

   a) አጠቃላይ - አንዳንድ ጊዜ ሁሉም የሙያ ሠራተኞች የሥራ ኃላፊነታቸዉን ለመወጣት ከመደበኛው የሥራ ቀን በተጨማሪ የተወሰነ ጊዜ የሚጠበቅባቸዉ መሆኑ ይታወቃል። እነዚህ መስፈርቶች በማንኛውም ጊዜ ቅድሚያ ይኖራቸዋል።

      የ MCPS ን የሥራ ኃላፊነት ለመወጣት በማይጠበቁ ሠዓቶች እና የቦርድ መርህ-Board Policy BBB ያልጣሰ የውጭ ሥራ መሥራት ስነምግባር-Ethics የጥቅም መጋጨት ተደርጎ አይቆጠርም።

   b) በትምህርት ቤት የሚሠሩ-የ MCPS ሠራተኞች ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ለመሥራት፣ ሠራተኞቹ በተመደቡበት ትምህርት ቤት(ቶች) በመከታተል ላይ ላሉ፣ ወይም ለሚከታተሉት ተማሪዎች ወላጆቻቸው ገንዘብ መክፈል ያለባቸው፣ በሚከፈለው ለአበል አግባብነት ባለዉ መጠን ከቦርዱ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ድርጅት ክፍያ መቀበል የለባቸውም። ይህም የሚያካትተው በዚህ ብቻ የሚወሰን ባይሆንም፣ ድራማ፣ዳንስ፣ ወይም የሙዚቃ ክፍሎች/ትምህርቶች ወይም ሥራዎችን ይሆናል።

   c) በትምህርት ቤት የማይሠሩ የ MCPS ሠራተኞች ተማሪዎቹ በሚመደቡበት ወይም ይመደቡበታል ተብሎ በሚታሰብበት ትምህርት ቤት የሥራው እንቅስቃሴ ከትምህርት ቤቱ ጋር የሚገናኝ ካልሆነ በስተቀር፣ ወይም እንቅስቃሴው ሠራተኛው(ዋ) በተመደበ(ች)በት ወላጆች መክፍል በሚኖርባቸው ትምህርት ቤት ከትምህርት ሠዓት በፊት/በኋላ የሚካሄድ ከሆነ ተማሪዎችን በማስተማር አይሳተፍም-አትሳተፍም።

      በ MCPS እና የ MCPS ን የትምህርት ተልእኮ በሚደግፉ የውጭ አጋር ድርጅቶች መካከል ከሚደረግ ሥምምነት ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ እና በዚህ ሥራ ላይ ያለ(ች) ሠራተኛ ተማሪዎቹ ወደሚሠማሩበት ፕሮግራም በሂደቱ የማይሣተፍ-የማትሣተፍ ከሆነ እያንዳንዱ ጉዳይ እየታየ በሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ አማካይነት ሊፀድቅ ይችላል።

2. የእረፍት ጊዜ ሥራ

   በክፍያ ወይም ያለክፍያ ከ MCPS በእረፍት ላይ ያለ(ች) ሠራተኛ፣ በእረፍት ላይ በሚሆንበት-በምትሆንበት ወቅት ከዋና የሥራ ኃላፊ በጽሑፍ ካልተፈቀደ በስተቀር በማናቸውም ደረጃ በ MCPS ሥራ እንዲሠራ-እንድትሠራ አይቀጠርም-አትቀጠርም።

3. በግል ማስጠናት እና የሠመር ካምፖች

   a) ለብቻ የትምህርት ክፍለ ጊዜ/በግል አስተማሪ የሚሰጥ ትምህርት

በግል ማስጠናት ማለት ከመደበኛ የትምህርት ቀን ውጪ በክፍያ የሚካሄድ ተጨማሪ፣ ልዩ፣ ወይም የማሟያ ማስጠናት/ትምህርት መስጠት ነው። (በተጫማሪ MCPS Regulation ABA-RB፣ ስለ ትምህርት ቤት ጎብኚዎች-School Visitors) ይመልከቱ

(1) በግል የማስጠናት ተግባር መደረግ ያለበት ከሠራተኛው የሥራ ሠዓት ውጪ ነው።

(2) የ MCPS ሠራተኛ በሚሠራበት-በምትሠራበት ትምህርት ቤት የሚማር-የምትማር ወይም ይማር-ትማር ይሆናል ተብሎ የታሰበ ተማሪን በግል አያስተምርም-አያስጠናም/አታስተምርም-አታስጠናም።

(3) እንደጉዳዩ ሁኔታ አንድ በአንድ እየታየ በሱፐርኢንተንደንቱ/ተወካዩ አማካይነት ተቀባይነት የሚሰጣቸው ልዩ ሁኔታዎች ይኖሩ ይሆናል —

   (a) ልዩ ሙያተኞች ለሚያስፈልጉት ስንክልና ካላቸው ልጆች ጋር የሠመር ፕሮግራሞች ሲኖሩ እና የልዩ ሙያተኞች እጥረት ባለበት ሁኔታ፣ በሠመር እንዲያስጠኑ ከወላጅ/ከሞግዚት በጽሑፍ የቀረበ ጥያቄ በ "Office of School Support and Improvement" ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ፣ የስፔሻል ኢጁኬሽን ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ፣ እና በርእሰመምህር ሲፀድቅ፣ ወይም

   (b) በ MCPS እና የ MCPS ን የትምህርት ተልእኮ በሚደግፉ የውጭ አካላት ጋር ከሚደረግ የሽርክና ሥምምነት መርሆዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ እና በማስጠናት ሥራ ላይ ያለ(ች) ሠራተኛ ተማሪዎቹ ወደሚሠማሩበት ፕሮግራም በሂደቱ የማይሣተፍ-የማትሣተፍ ከሆነ።

(4) ወደ MCPS ፕሮግራም ለማስገባት ተማሪዎችን ለፈተና እንዲዘጋጁ በማስጠናታቸው ምክንያት ሠራተኞች የ MCPS አካል ካልሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ ማካካሻ አይቀበሉም።

(5) የ MCPS ሠራተኞች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት ላይ የማስጠናት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ይህንን ደምብ "MCPS Regulation KGA-RA" መከተል ይኖርባቸዋል Community Use of Public Schools።

b) የሠመር ካምፖች እና ከትምህርት ሠዓት በፊት ወይም በኋላ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች

በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ የሠመር ካምፖች እና ከትምህርት ሠዓት በፊት ወይም በኋላ ስለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች

ሠራተኞች እነዚህን መመሪያዎች መከተል ይኖርባቸዋል የሠመር ካምፓችን/ፕሮግራሞችን/እንቅስቃሴዎችን ለሚያካሄዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ መመሪያ - Guidelines for Montgomery County Public Schools Conducting Summer Camps/Programs/Activities የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የአትሌቲክስ መምሪያ መጽሐፍ እና የሜሪላንድ የህዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአትሌቲክ ማህበር

መምሪያ መጽሐፍ - MCPS Athletic Handbook and Maryland Public Secondary Schools Athletic Association Handbook

(2) በትምህርት ቤት ስፖንሰር ያልተደረጉ የሠመር ካምፖች እና ከትምህርት ሠዓት በፊት ወይም በኋላ ስለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች:-

(a) ሠራተኞች በማናቸውም የስፖርት ካምፖች ወይም ልዩ ሙያ በሚሠለጥኑበት ካምፕ፣ ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች በፊት ወይም በኋላ ሠራተኛው(ዋ) በሚያስተምርበት-ወይም ለወደፊት ያስተምርበታል-ታስተምርበታለች ተብሎ በሚታሰብበት፣ በተመሣሣይ ስፖርት የቡድን አሠልጣኝ በሚሆንበት-በምትሆንበት፣ ወይም ለተወዳዳሪ ቡድን ተማሪዎችን በሚመርጡበት ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ማስተማር አይኖርባቸውም።

(b) ሠራተኞች የትምህርት ቤት ፋሲሊቲን ወይም የትምህርት ቤት ሜዳዎችን ለመጠቀም በማህበረሰብ የፋሲሊቲ አጠቃቀም በኩል ማመልከት ይኖርባቸዋል።

(c) ሁሉም ማህበረሰብ እንዲጠቀምበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ሠራተኞች የትምህርት ቤትን መስርያ መሣሪያዎች እና አቅርቦቶችን መጠቀም አይኖርባቸውም።

E. ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት

በሠራተኛ የፈጠራ ሥራ ውጤት የሚዘጋጁ አቅርቦቶች፣ የሥራ መሣሪያዎች፣ ወይም እቃዎች/ቁሳቁሶች

1. በ MCPS የሚከናወን ግዢ

ሠራተኞች ከተቀጠሩበት የ MCPS ሥራቸው እና ኃላፊነታቸው ጋር ምንም አይነት ተያያዥነት ሣይኖር እና ምንም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን ሪሶርሶች፣ ጊዜ፣ ወይም ማቴሪያሎችን ሳይጠቀሙ በግላቸው የሠሯቸውን/ያመረቷቸውን አቅርቦቶች፣ መሥርያ መሣሪያዎች፣ ወይም ማቴሪያሎች/ቁሳቁሶች ማንኛውንም ለሌላ እቃ ግዢ የሚደረገውን አሠራር መሠረት ባደረገ ሁኔታ MCPS ሊገዛ ይችላል።

a) የሠራተኛ የፈጠራ ሥራ ውጤት አቅርቦቶች፣ የመሥሪያ መሣሪያዎች፣ ወይም ቁሳቁሶች-ማቴሪያሎች የቦርድ መርህ-Board Policy BBB መሠረት ስነምግባር-Ethics እና ሌሎች በሥራ ላይ ያሉ የአሠራር ደምቦችን መሠረት በማድረግ ለግዢ መመረጥና መፅደቅ አለባቸው።

b) እቃው በሥራ ላይ ያለ(ች) ወይም የቀድሞ የሥራ ባልደረባ የፈጠራ ሥራ ውጤት በመሆኑ እንዲመረጥ ወይም እንዳይመረጥ ምክንያት መሆን የለበትም።

2. የጥቅም ግጭትን ለማስወገድ፣ ሠራተኞች የትዳር ጓደኞቻቸው፣ ዘመድ፣ አማቾች፣ ወይም ማንኛውም የጾታ ግንኙነት ካላቸው ሰው ግላዊ ጥቅም ከሚያስገኝ ማናቸውም አይነት የግዢ ውሳኔዎች፣ ምርጫ ማከናወን፣ ወይም ሌላ ውሳኔ የመስጠት ሒደቶች ራሳቸውን ማግለል አለባቸው።

3. የ MCPS ንብረት

   a) የ MCPS ን ጊዜ፣ ፋሲሊቲዎችን፣ ቁሳቁሶችን፣ ወይም የ MCPS ሪሶርሶችን በመጠቀም ወይም የሠራተኛው(ዋ) የሥራ ድርሻ-ሃላፊነት ጋር በተያያዘ ምክንያት በአንድ የ MCPS ሠራተኛ በተናጠል፣ ወይም ከሌሎች የ MCPS ሠራተኞች ጋር በህብረት የፈጠራ ችሎታ የተዘጋጁ አቅርቦቶች፣ የመሥሪያ መሣሪያዎች፣ ወይም ማቴሪያሎች-ቁሳቁሶች ንብረትነታቸው የ MCPS ይሆናል።

   b) ሥራው በከፊል የግል እና ከፊሉ የህዝብ በሚሆንበት ሁኔታ ፈጠራውን ላከናወነ(ች) ሰው ስለሚደረግ ክፍያ በዋና የሥራ ኃላፊ/ተወካይ አማካይነት የቅድሚያ ዝርዝር ስምምነት መፅደቅ ይኖርበታል።

F. የባለቤትነት ሙብት ወይም ምስጢራዊ መረጃዎችን ስለመጠቀም

1. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ሃላፊነት ምክንያት የያዘ(ች)ውን የተማሪዎችን እና/ወይም የወላጅ/የሞግዚት መረጃ ዝርዝር በ "MCPS Regulation JOA-RA" የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም ሌላ ሰው ወይም የንግድ ድርጅት መስጠት አይችልም-አትችልም የተማሪ ሪኮርዶች-Student Recordsእና MCPS Regulation AFA-RA፣Research and Other Data Collection Activities in Montgomery County Public Schools።

2. ሠራተኞች የ MCPS ሠራተኛ በመሆናቸው ምክንያት የሚያኙትን ለህዝብ ይፋ ያልተደረጉ ድርጅታዊ መረጃዎችን መግለጽ ወይም መጠቀም አይኖርባቸውም። በማንኛውም የተለየ ሁኔታ ተቀባይነት የሚኖር ከሆነ በዋና የሥራ ኃላፊ/ተወካይ አማካይነት በቅድሚያ መፅደቅ ይኖርበታል።

## V. ደምብ አለማክበር-ጥሰት

ይህንን ደምብ የመጣስ ሁኔታ ከተጠረጠረ በዋና የሥራ ኃላፊ/ተወካይ አማካይነት አስቸኳይ ምርመራ ለማድረግ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሠራተኛው(ዋ) ይህንን ደምብ እንደጣሰ(ች) ከተረጋገጠ፣ የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድበ(ባ)ት ይችላል፣ በሚመለከታቸው የቦርድ መርሆች፣ የ MCPS ደምቦች፣ እና የ MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ደምብ በሚፈቅደው መሠረት፣ የተግሣጽ እርምጃን ጨምሮ፣ እገዳ፣ ወይም ከሥራ የማሰናበት እርምጃ ሊያስወስድ ይችላል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Annotated Code of Maryland, Maryland Public Ethics Law Article, Subtitle 8; Code of Maryland Regulations, §13A.06.03.04.G; MCPS Employee Code of Conduct; Handbook of the Maryland Public Secondary Schools Athletic Association; Guidelines for Montgomery County Public Schools Conducting Summer Camps/Programs/Activities

ስለ ደንቡ ታሪክ፡- አስቀድሞ ደንብ ቁ. 490–1, December 29, 1978 (directory information updated); revised November 16, 2000; revised April 9, 2002; revised April 17, 2013; revised July 31, 2017.